# ሰሞነኛ (ልዩ ዕትም)

**« ህዝባችን ይመርጣል ፤የነውጥ ሀይሉም ያፍራል:: »**

**በሎስ አንጀለስ የኢትዮጵያ ቆንስላ**

**ጄኔራል ጽ/ቤት**




**Consulate General of Ethiopia**

**3460 Wilshire Blvd #308**

**Los Angeles, CA 90010**

**Tel: 213 365 6651 Fax: 213 365 6670**

www.ethioconsulatela.org


**ግንቦት /2002**

**April/2009**



# ህዝባችን ይመርጣል ፣
# የነውጥ ሀይሉም ያፍራል::

በኢትዮጵያ የሚካሄደው አራተኛው  አገራዊ ምርጫ የመቋጫ ምዕራፍ እንሆ የፊታችን እሁድ ግንቦት 15 ቀን 2002 ነው :: በምርጫው የሚሳተፉ የፖለቲካ ድርጅቶች ያራመዱት ዓላማና ፖሊሲ፣የሰነቁት ግብና የወደፊት ብሩህ ተስፋ በህዝብ የድምፅ ሚዛን የሚሰፈርበት ዕለት ነው:: ለህዝቡ ያቀረቡት ቅስቀሳ ፣ያካሄዱት ስብስባ ፣የተከናወኑ ክርክሮች ሁሉ በአገራችን የዴሞክራሲያዊ ህገመንግሰት የበላይነት  አንዱ መገለጫ ነውና፣ በበጎ ጎኑ የሚታይና  ብሎም ከምርጫው ማግስት ይቀጥል ዘንድ የሁሉንም ትጉህ ተሳትፎ የሚጠይቅ ይሆናል::

ምርጫ የአንድ አፍታ ኩነት ሳይሆን አዲስ የፖለቲካ ባህልን የሚገነባ ፣ከነውጥ ይልቅ ሰላምን የሚናኝ ፣ልማትንና ዕድገትን በጠንካራ መሠረት ላይ የሚያዋቅር፣ ብሎም በዕኩልነት ላይ አገራዊ አንድነትን ለማምጣት የሚያስችል ፍቱን መንገድ ነው:: እንሆ ለአራተኛ ጊዜ በኢትዮጵያ የሚካሄደው አገራዊና ብሄራዊ ምርጫ  ዓላማዎቹና ግቦቹ የህዝብ የበላይነትን ማረጋገጥ፣እኩልነትን ማምጣት፣ ሰላምን አስተማማኝ ማድረግና ልማታዊ ግስጋሴን ማስቀጠል ነው::

ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት የአገራችን ህዝቦች አስተሳሰብ ልህቅና፣ፅናት ፣ብሩህ ተስፋና ቀጣይ ራዕይ ዳግም በሚዘከርበት በዚህ ምርጫ ላይ ጨለምተኛ ብዕራቸውን የቀረፁ፣ነውጠኛ  አንደበታቸውን የሳሉ፣በሞገደኛ አስተሳሰባቸው ቆመው የቀሩና ኢትዮጵያውያን በዴሞክራሲና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድ ጠንካራ የፖለቲካ ማህበረሰብ ለመገንባት የሚያደርጉትን እርምጃ ትቢያ ለማልበስ በመራወጥ ላይ ይገኛሉ:: በተንኮል የተካኑ ሃይሎች ቢቻላቸው ግርግር በመፍጠር ካለያም የሟርት ብዕራቸውን እንደተለመደው በመሳል ላይ ናቸው::

በተለይ ዘወትር የኢትዮጵያ አገራዊ ግስጋሴ ከሚኮሰኩሳቸው በደስታዋ ለሚሳለቁ፣በድህነቷ ከሚያፌዙ የውጭ ጋዜጠኞች መካከል በቁንጮነት የሚታወቀው Jeffery Littleman ቀን አሰልቶና ነባርተኛውን ቂም ቋጥሮ የአገራችን ህዝቦች ለዕድገት ግስጋሴያቸው ያግዛል ብለው በመረጡት የዴሞክራሲ ምርጫ ሂደት ላይ በዘረኛ ቀለም የተነከረውን ብዕሩን አሹሏል፡፡የጋዜጠኛው መነሻም ሆነ መደምደሚያ ልኬታ ኢትዮጵያውያንም ሆኑ ሌሎች አፍሪካውያን ለዴሞክራሲ ባዕድ ናቸው ፣ምርጫ ቢሉም የፌዝ ነው፣በመሆኑም የአደጉና የተመነደጉ አገሮች ሊገሯቸው፣ ሊቆጣጠሯቸውና ሊያርቋቸው ይገባል የሚል ነው፡፡

በሌላም በኩል በዚህ በውጭ አገር በሚገኘው የጥላቻ ፖለቲከኛ ሀይል የሚወጡ ፅሁፎች የሚያሳዩት ምርጫውን ኢህአዴግ ሊያሸነፍ መቻሉን ተቀብለው፣ ነፃና ዲሞክራሲያዊ አልነበርም ሊያሰኝ የሚያስችሉ ህፀፆችን በመፈለግና ጥላሸቶችን በመቀባት ላይ ያተኮሩ እንደሆነ እነደሆነ ማየት ይቻላል፡፡ይህም በምርጫው ዋዜማ፣ ዕለትና ማግስት ምርጫውን የሚፈታተኑ ተግባራትን በመፈፀም ታዓማኒነቱን ሊያጎድፍ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወንን ያካትታል፡፡ ይህ ሁሉ ሆኖ ካልተሳካም ድሮም ብለናል በሚል መንፈስ የሚነሳ ትንታኔ በሰፊው መርጨት ሲሆን ይሄው አዲስ የተባለው ስልት ደግሞ ገዥው ፓርቲ ሰፊ ወከባና እንግልት በተቃዋሚዎች ላይ እየፈፀመ ባለበት፣የፕሬስ አፈና እየተካሄደ ባለበት ፣ታዛቢዎች ምርጫው መታዘብ እንዳይችሉ እየተከለከሉ የገዢውን ፓሪቲ አሸናፊነት መለወጥ አይቻልም ስለዚህ ምርጫው ከወዲሁ ተአማኒነት የለውም የሚል ቅስቀሳን ማካሄድ ነው፡፡

በመጭዎቹ ጥቂት ቀናት የምርጫውን ታዓማኒነት የሚፃረሩ ተግባራት ለማከናወን ከግራ ቀኝ በጊዜአዊ ዝምድና ከሻቢያ ጋር ተቧድነው የሚውተረተሩ ቢሆንም የኢትዮጵያ ህዝቦች የጀመሩትን የዴሞክራሲያዊ መንገድ የሚያሰናክሉ አይሆኑም፡፡

በመሆኑም በውጭ የምንገኝ ለአገራችን ደህንነትና ለህዝባችንን ስላምና ብልፅግና በጎ የምንመኝ ኢትዮጵያውያንና የዲሞክራሲ ወገኖች በአፍራሽ ሀይሎች በተቀነባበረ መልክ ሊያራምዱት የሚከጅሉትን ሴራ ሁሉ በጋራ እንድናከሽፍ ደግመን ጥሪያችን እያቀረብን ወሳኝ በሆነው በህዝባችን ሀይል ተማምነን ህዝባችን ይመርጥ ዘንድ እናበረታታ፡፡ የነውጥ ጎራውን እንታገል! የብድር ፀሀፊውን ወገንም አናሳፍር፡፡